# በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር

# የሽርክና (የፓርትነርሺፕ) አፈጻጸም መመሪያ

**513/2013**

ህዳር/2009

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር

# የመንግሥትና የግል ሽርኪና አፈጻጸም መመሪያ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው ለልማቱ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱና በልማት ስትራቴጂው የተቀመጠውን ዓላማ ለማሣካት ከግል ባለሀብት ጋር አብረው በመሥራት የእውቀትና የቴክኖለጂ ሽግግር እንዲያደርጉ በዚህም ምርታማነት ማሳደግ በማስፈለጉ፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከግሉ ባለሀብት ጋር የሚገው ሽርክና (ፓርትነርሺፕ) ግልጽነትን፣ ፍትሐዊነትንና ተቀባይነት ያለው ስርዓት በመዘርጋት የግሉን ዘርፍ አቅም ለልማት እንዲውል ለማበረታታት የሚያግዝ አሠራር መዘርጋት በማስፈለጉ፣

ሽርኪና ለማስገባት የሚደረግ ቅድመ ዝግጅቶችን፣ የሽርኪና የማወዳደርና የመምረጥ ሂደትና ከምስረታ በኋላ ያሉ የትግበራ፣ የአፈፃፀምና የክትትል ሥራዎችን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል ግልጽ አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916 /2008 እና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር የወጣ አዋጅ ቁጥር 146/1991 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍልአንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህመመሪያ ሽርክና የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 513/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንዳቅደም ተከተሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው::
2. "ሽርኪና" ማለት ከመንግሥት ጋር አብሮ ለመሥራትና ለማልማት፣ የማኔጅመንት ኮንትራት፣ ኪራይ (Lease)፣ ኮንሴሽን (concession)፣ እና ቦት (BOT)፣ ቡት (BOOT)፣ሮት (ROT) እና ዲቢኦ (DBO) ሊያካትት ይችላል::
3. "ሽሪክ" ማለት በመንግሥት የልማት ሥራ ለመሣተፍ የሚፈልግ የልማት ወይም የሥራ ተባባሪ ነው::
4. "የጋራ ልማት አክሲዮን ማህበር ምስረታ" ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 መሠረት የተቋቋመ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ወይም መንግሥት የአክሲዮን ድርሻ ባለቤትነት ያለበት ደርጅት ወይም ወደ ተግባር እንዲሸጋገር የተወሰነ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክት የግልና በድርጅት መካከል የንግድ ማህበር ለመመስረት የሚደረግየልማት ስምምነት ነው::
5. "የማኔጅመንት ኮንትራት" ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 የተቋቋመ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር የወጣ አዋጅ ቁጥር 146/1991 መንግሥት ሙሉ በሙሉ የአክሲዮን ድርሻ በያዘበት ድርጅት ከግል ወይም ድርጅት በውል ለተወሰነ ጊዜ የማኔጅመንት ሥራዎችን ለማሠራት የሚፈጽመው ውልነው:: የማኔጅመንት ኮንትራቱ ወደ አፈፃፀም እንዲሸጋገር ውሣኔ ያገኘን ፕሮጀክትም ሊያካትት ይችላል::
6. "ኮንትራክተር" ማለት የመንግሥታዊ የልማት ድርጅትን ወይም አክሲዮን ማህበርን በማኔጅመንት ኮንትራት ተወዳዳሪነታቸውንና የገበያ አድማሣቸውን እንዲያሰፋ እና ትርፋማ እንዲያደርጋቸው ለተወሰነ ጊዜ ቆይታ ከሚኒስቴሩ ጋር ውል የሚገባ ነው::
7. "ኮንትራት" ማለት መብቶችን፣ ጥቅሞችንና ግዴታዎችን በተመለከተ በውል ሰጪና በውል ተቀባይ መካከል ተስማምተው የሚፈራረሙበት የስምምነት ሰነድ ነው::

8. "የማኔጅመንት ኮንትራት ክፍያ" ማለት በውል ስምምነት መሠረት የማኔጅመንት አገልግሎት ለሰጠ ሰው የሚከፈል የክፍያ (Management Fee) ዓይነት ነው፡፡

9. "ኪራይ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 25/84 መሠረት የተቋቋመ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ወይም የድርጅት ቅርንጫፍ ለተወሰነ ጊዜ በውል ለመስጠት በሚኒስቴሩና በተከራይ መካከል የሚፈጸም በህግ ተቀባይነት ያለው ውል ነው፡፡

10. "ተከራይ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘን ድርጅት ወይም የድርጅት ቅርንጫፍ በኪራይ ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ ኪራይ እየከፈለ የመጠቀም መብት እንዲያገኝ ከሚኒስቴሩ ጋር የሚዋዋል ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው፡፡

11. "አከራይ" ማለት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘን ድርጅት ወይም የድርጅት ቅርንጫፍ በኪራይ ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ ተከራዩ እንዲጠቀምበት የማስተላለፍ መብት ያለው ሚኒስቴሩ ነው፡፡

12. "የልማት ድርጅት" ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 አንቀጽ 2 (3) የተሰጠው ትርጓሜ ይኖራል፡፡

13. "አክሲዮን ማህበር" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ አክሲዮን ማህበር ነው፡፡

14. "ቦርድ" ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ2 መሰረት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚቋቋም አካል ሲሆን የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው በአዋጅ ቁጥር916/2008 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የሚሠየምና መንግሥትን ወክሎ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሥራ እንቅስቃሴ የሚከታተል የስራ አመራር ቦርድ ወይም በሚኒስቴሩና በውጭ ተባባሪው ወገን በጋራ የሚሠየም የሥራ አመራር ቦርድ ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

15. "ኮንሴሽን" ማለት የረዥም ጊዜ ኪራይ ውል ሲሆን በተጨማሪም ተከራዩ ኢንቨስትመንት የማካሄድ ግዴታ የሚኖርበት ነው፡፡

16. "ቦት" /BOT (Build Operate Transfer) ይህ የመንግስት ፕሮጀክቱን የግል ባለሐብቱ የመገንባት፣ ለተወሰነ ጊዜ በመምራት የመጠቀም ከረጅም ጊዜ በኋላ ንብረቱ ለመንግስት የሚተላለፍበት የትብብር ዓይነት ነው፡፡

17. "ቡት" /BOOT (Build Own Operate Transfer) ይህ የመንግስት ፕሮጀክቱን የግል ባለሐብቱ በራሱ ፋይናንስ የመገንባት፣ ባለቤት የመሆን፣ ለተወሰነ ጊዜ በመምራት

የመጠቀም ከረጅም ጊዜ በኋላ ንብረቱ ለመንግስት የሚተላለፍበት በአገልግሎት ላይ የሚደረግ የትብብር ዓይነት ነው።

18. "ሮት" /ROT (Rehabilitate Operate Transfer) ይህ ነባር የመንግስት መሠረተ ልማቶችን የግል ባለሀብቱ በራሱ ፋይናንስ የማሻሻል፣ የመጠገንና የማደስ ስራን በማከናወን ለተወሰነ ጊዜ በመምራት የመጠቀም ከረጅም ጊዜ በኋላ ንብረቱ ለመንግስት የሚተላለፍበት የትብር ዓይነት ነው።

19. "ዲቢኦ" (DBO) (Design Build Operate) ይህ የመንግስት ፕሮጀክቱን የግል ባለሀብቱ የመገንባት፣ ለተወሰነ ጊዜ በመምራት የመጠቀም ከረጅም ጊዜ በኋላ ንብረቱ ለመንግስት የሚተላለፍበት የትብብር ዓይነት ነው።

20. "የረጅም ግዜ የኪራይ ውል" ማለት ከ5 ዓመት በላይ ለሚቆይ ግዜ የሚደረግ የኪራይ ውል ነው።

21. በዚህመመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

### 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህመመሪያ ለሚኒስቴሩ በቀጥታ ተጠሪ በሆኑ ልማትድርጅቶች /አክሲዮንማህበራት እና አዳዲስ በሚቋቋሙ ፕሮጀክቶች ላይተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ሽርኪና የማስገባት ሥርዓት

ሽርኪና በሚኒስቴሩ ወይም በሽሪክበሚቀርብ ፍላጎት መነሻነት ሊመሰረት ይችላል።

### 4. በሚኒስቴሩ ፍላጎት ሲቀርብ፤

ሽሪክየመፈለጉና የማስገባቱ ሥራ በሚኒስቴሩ ተነሣሽነት (initiative) የሚቀርብ ከሆነ የሚከተሉትን አማራጮች መጠቀም ይቻላል።

### 4.1. በጨረታ ስለመጥራት

የሽሪክ (ፖርትነር) ፍለጋ የሚከናወነውበግልጽ ጨረታ ጥሪ በማድረግ ይሆናል።

4.4.5.5. የምርታማነትና የምርት/አገልግሎት ጥራት ማሻሻል የሚችል፣

4.4.5.6. የካፒታል አቅም ማሣደግ የሚችል፣

4.4.5.7. የምርት/አገልግሎት አድማስ ወይም የምርት ስብጥርን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ ማሣደግ/ማሻሻል የሚችል፣

4.4.5.8. ሀብትን የተሻለ ዕሴት በሚያስገኝ መልኩ ለመጠቀም የሚችል፣

4.4.5.9. ለአካባቢ ጥበቃ ልዩ ትኩረት መስጠት እና የማህበራዊ ሃላፊነትን በብቃት ለመወጣት ትኩረት መስጠት የሚችል፣

4.4.5.10. በረጅም ጊዜ በሚመለስ equity investment ላይ መሳተፍ የሚችል፤

4.4.6 የግምገማ መስፈርቶቹ እንዳግባቡ ከላይ የተገለጹት ሁሉም ወይም በከፊል እንደ ጨረታው ባህሪ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ።

4.4.7 በአንቀጽ 4.4.3 መሰረት ከአንድ የበለጠ ሽሪኮች (ፓርትነሮች) በቀጥታ ወይም በማስታወቂያ ጥሪ በሚቀርቡበት ጊዜ የተሻለውን ለመምረጥ የሚያስችሉ መመዘኛዎችና ክብደታቸው አስቀድመው ተዘጋጅተው ተወዳዳሪዎቹ እንዲያውቋቸው ይደረጋሉ።

4.4.8 በማናቸውም መንገድ የሚገኝ የሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) ጥያቄ ውጤት የሚኖረው በሚኒስቴሩ ውሳኔ ተሰጥቶበት ሲጸድቅ ነው።

## 5. በሽሪኩ (በፓርትነሩ) ፍላጎት ጥያቄ ሲቀርብ

አንድ ፓርትነር ከመንግስት ጋር አብሮ ለመስራት ፍላጎቱን ለሚኒስቴሩ ሊያቀርብ ይችላል።ሽሪኩ (ፓርትነሩ) የሚያቀርበው ፕሮፖዛል የሚከተሉትን ይይዛል።

### 5.1. የጋራ ልማት ኮንትራት ምስረታ ሲሆን

5.1.1 ስለ ሽሪኩ (ፓርትነሩ) ማንነት፣ ዜግነት፣ ቋሚ አድራሻ፣ የሥራ ሥምሪት፣

5.1.2 ለሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) የሚፈልገው የሥራ መስክ ወይም የልማት ድርጅት ወይም ፕሮጀክት፤

5.1.3 የሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) ዓላማ፣ ይዘትና ከተግባራዊነቱ የሚጠበቅ ውጤት፤

5.1.4 ዝርዝር የቢዝነስ ፕላን ወይም የአዋጪነት ጥናት፤ ወይም የፕሮጀክት ሀሣብ፤

5.1.5 የሚሣተፍበት የአጋርነት ዓይነት (ኢኪቲ ወይም ከኢኪቲ ውጪ) እና እንዲኖረው የሚፈልገው ድርሻና የመዋጮ መጠን፤

5.1.6 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5.1(ከ5.1.1 እስከ 5.1.2) የተገለጹትን በመጀመሪያ ማሟወቅ ያለበት ሲሆን ከ5.1.3 እስከ 5.1.5የተገለጹትን በጨረታ በሂደት ወይም የመጨረሻ የሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) ውል ከመፈረሙ በፊት መሟላት አለበት፡፡

## 5.2. የማኔጅመንት ኮንትራት ምስረታ ሲሆን

5.2.1 . ስለኮንትራክተሩ ማንነት፣ ዜግነት፣ ቋሚ አድራሻ፣ የሥራ ሥምሪት፣

5.2.2. በኮንትራክተርነት ለመግባት የሚፈልገው የሥራ መስክ ወይም የልማት ድርጅት ወይም ፕሮጀክት፤

5.2.3. የኮንትራክተሩ ዓላማ፣ ይዘት፣ ቆይታ ጊዜና ከተግባራዊነቱ የሚጠበቅ ውጤት፤

5.2.4. ኮንትራክተሩ በሚያመለክተው የሥራ ዘርፍ ከዚህ ቀደም የሰራና ያስተዳደረ ሆኖ በዘርፉ ያለው የቴክኒካልና የማኔጅመንት ብቃት፣

5.2.5. ዝርዝር የቢዝነስ ፕላን ወይም የአዋጪነት ጥናት፤ ወይም የፕሮጀክት ሀሣብ፤

5.2.6. የኮንትራት የአፈጻጸም አመልካቾች(performance indicators) እና የሚከፈለው ክፍያ (Management Fee)፣

5.2.7. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ5.2 (ከ5.2.1እስከ5.2.4) የተገለጹትን በመጀመሪያ ማሟወቅ ያለበት ሲሆን ከ5.2.5 እስከ 5.2.6 የተገለጹትን በጨረታ በሂደት ወይም የመጨረሻ የሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) ውል ከመፈረሙ በፊት መሟላት አለበት፡፡

## 5.3. የኪራይ ኮንትራት ምስረታ ሲሆን

5.3.1. ስለተከራዩ ማንነት፣ ዜግነት፣ ቋሚ አድራሻ፣ የሥራ ሥምሪት፤

5.3.2. ተከራዩ የሚፈልገው የሥራ መስክ ወይም የልማት ድርጅት ወይም ፕሮጀክት፤

5.3.3. የኪራዩ ዓላማ፣ ይዘት፣ ቆይታ ጊዜናከተግባራዊነቱ የሚጠበቅ ውጤት፤

5.3.4. ተከራዩ በሚያመለክተው የሥራ ዘርፍ ከዚህ ቀደም የሰራና ያስተዳደረ ሆኖ በዘርፉ ያለው የቴክኒካልና የማኔጅመንት ብቃት፣

5.3.5. ዝርዝር የቢዝነስ ፕላን ወይም የአዋጪነት ጥናት፤ ወይም የፕሮጀክት ሀሣብ፤

5.3.6. የሚከፍለው የኪራይ መጠን፤

5.3.7. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ5.3(ከ5.3.1እስከ 5.3.4) የተገለጹትን በመጀመሪያ ማሣወቅ ያለበት ሲሆንከ 5.3.5አሰከ 5.3.6) የተገለጹትን በጨረታበሂደት ወይም የመጨረሻ የሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) ውል ከመፈረሙ በፊት መሟላት አለበት::

**5.4. የኮንሴሽን (concession) ምስረታ ሲሆን**

5.4.1 ስለሽሪኩ (ፓርትነሩ) ማንነት፣ ዜግነት፣ ቋሚ አድራሻ፣ የሥራ ሥምሪት፣

5.4.2. ለሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) የሚፈልገው የሥራ መስክ ወይም ፕሮጀክት፤

5.4.3. የሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) ዓላማ፣ የስራው ስፋት፤ መጠን እና ከተግባራዊነቱ የሚጠበቅ ውጤት

5.4.4. ተከራዩ በሚያመለክተው የሥራ ዘርፍ ከዚህ ቀደም የሰራና ያስተዳደረ ሆኖ በዘርፉ ያለው የቴክኒካልና የማኔጅመንት ብቃት፣

5.4.5. ዝርዝር የቢዝነስ ፕላን ወይም የአዋጪነት ጥናት፤ ወይም የፕሮጀክት ሀሣብ፤

5.4.6. ለሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) የሚፈልገው የሥራ መስክ ወይም ፕሮጀክት የስምምነት ዋጋ፤ የአከፋፈል ሁኔታ

5.4.7. ለሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) የሚፈልገው የሥራ መስክ አጀማመር ሂደት፤ የስራው ሂደት ክትትልና ርክክብ

5.4.8. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5.4 (ከ5.4.1 እስከ 5.4.5) የተገለጹትን በመጀመሪያ ማሣወቅ ያለበት ሲሆንከ 5.4.5 አሰከ 5.4.7) የተገለጹትን በጨረታ በሂደት ወይም የመጨረሻ የሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) ውል ከመፈረሙ በፊት መሟላት አለበት::

## 6. በፓርትነሩ የሚቀርብ የሽርኪና (ፓርትነርሽፕ) ጥያቄ የሚስተናገድበት ስርዓት

6.1 አንድ ሽሪክ (ፖርትነር) በሽርኪና ለመሥራት ጥያቄ ለሚኒስቴሩ በፅሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

6.2 የአንድ ሽሪክ (ፖርትነር) በሽርኪና ጥያቄ ለሚኒስቴሩ ቀርቦ ተቀባይነት ካገኘ ሌሎች ተወዳዳሪዎች ሊሳተፉበት የሚችል እድል ለመስጠት በአንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ ከ4.1 እስከ 4.3 ከተጠቀሱት የጨረታ ስልቶች ከሦስቱ በአንዱ እንዲስተናገድ ሊወሰን ይችላል፡፡

6.3 ሽሪኩ (ፖርትነሩ) ላቀረበው ፕሮፖዛል ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከሚኒስቴሩ ምላሽ በፅሁፍ ይሰጠዋል፡፡ ይህ ጊዜ በቅድሚያ ከሽሪኩ (ፖርትነሩ) ሊቀርቡ የሚገባቸውን ተጨማሪ ማብራሪያዎች ወይም ማስተካከያዎች የተደረገበትን ጊዜ ያካትታል፡፡ ሆኖም ሽሪኩ (ፓርትነሩ) ተቀባይነት ባለው ምክንያት ማብራሪያዎች ወይም ማስተካከያዎች ማቅረብ ከልቻለ በሚኒስትር ውሳኔ ለተጨማሪ አንድ ወር ጊዜ ሊራዘም ይችላል፡፡

6.4 ሽሪኩ (ፖርትነሩ) ያቀረበው ፕሮፖዛል ተቀባይነት የሌለው ከሆነ በዘርፉ የተገመገመው ውጤቱ በዘርፉ ለሚኒስቴሩ ቀርቦ መልስ ይሰጣዋል፡፡

6.5. ሽሪኩ (ፓርትነሩ) በተሰጠው ምላሽ ካልረካ ቅሬታውን ለሚኒስትሩ አቅርቦ የመጀመሪያውን ውሳኔ ሊያስቀይር የሚያስችል በቂ ምክንያት ከተገኘ ውሳኔው ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 7. የሽርኪና ድርድር፣

7.1. የጨረታ ሽያጭ ወይም የድርድር ኮሚቴው በሽሪክነት በጨረታ ወይም በቀጥታ ከተመረጡት ጋር ድርድር ያደርጋል፡፡

7.2. የድርደር ሂደቱ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የድርድር አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሽርኪና ምስረታና ውጤት

### 8.ሽሪኩ (ፓርትነሩ) የሚሳተፍባቸው አማራጮች

ሽሪኩ ፓርትነሩበሚከተሉት አማራጮች ሊሳተፍ ይችላል።

### 8.1 የጋራ ልማት ኮንትራት ምስረታ ሲሆን

#### 8.1.1 በኢኩቲ መዋጮ (Equity Contribution)

8.1.1.1. ሽሪኩ በአይነት ወይም በገንዘብ የሚመዘን መዋጮ ይዞ የሚገባበት ሲሆን የመዋጮው አይነት ገንዘብ፣ መሳሪያ፣ የአእምሮና የኢንዱስትሪ ንብረት፣ የቴክኖሎጂ እውቀት (know-how) ወይም ሌላ ቋሚ ወይም ተንቀሳቃሽ ንብረት ሊሆን ይችላል።

8.1.1.2. በአይነት የሚዋጣው ሀብት አግባብ ባለው ህጋዊ አሰራር ተተምኖ የገንዘብ ዋጋ ሊኖረው ይገባል።

8.1.1.3.በኢኩቲ መዋጮ የሚመሰረተው የጋራ ልማት ነባር ድርጅትን በመዋጣት፣ ተጠንቶ ባለ ፕሮጀክት ላይ መዋጮ በማዋጣት እና አዲስ የሚጠና ፕሮጀክት ሊሆን ይችላል።

8.1.1.4. አዲስ ፕሮጀክት ሲሆን በአጋሩ ወይም በሚኒስቴሩ የፕሮጀክት ጥናት ተጠንቶ ይቀርባል።

#### 8.1.2. በኢኩቲ ያልሆነ መዋጮ (Non-Equity Contribution)

8.1.2.1 ይህ በንግድ ምልክት /ብራንድ፣ በላይሰንስ፣ በወጪ ገበያ (access to foreign market) በንብረት ወይም በይዞታ ኪራይ (Premise renting) በቴክኒክ/ቴክኖሎጂ ድጋፍ፣ ሊከናወን የሚችል ሆኖ በልማት ድርጅቱ የባለቤትነት ይዞታ ላይ በሙሉም ሆነ በከፊል ለውጥ የሚያመጣ አይሆንም።

8.1.2.2 የአንድን ልማት ድርጅት ቀጥር ግቢ /ፋሲሊቲ፣ በመጠቀም በውል ላይ የተመሰረተ የባለቤትነት ለውጥ የማያመጣ አጋርነት ሊመሰረት ይችላል፡፡

8.1.2.3 በዚህ አንቀጽ በንኡስ ቁጥር 8.1.2.1 በተገለጸው መሰረት የሚመሰረተው ሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) እንደ ሁኔታው ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ሊሆን ይችላል፡፡

8.1.3. በሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) ምስረታ ወቅት ነባሩ ድርጅት ካለው ንብረት በተጨማሪ መዋዕለ ማቅረቡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**8.2 የማኔጅመንት ኮንትራት ሲሆን**

8.2.1. የኮንትራት ጊዜ በማኔጅመንት ኮንትራት የሚገለጽ ሆኖ እንዳ አስፈላጊነቱ ከ2-5 አመት ይሆናል፡፡ ውል አፈጻጸሙ አጥጋቢ ሆኖ ሲገኝ የኮንትራት ጊዜው ለተጨማሪ አንድ የውል ዘመን ሊራዘም ይችላል፡፡

8.2.2. የአከፋፈል ሁኔታው በዝርዝር በውሉ የሚገለጽ ሆኖ ከአፈጻጸም መለኪያዎች ጋር በተያያዘ የሚከተሉት የአከፋፈል አይነቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

ሀ. የተወሰነ ክፍያ (fixed fee)

ለ. የስኬት ክፍያ(Success fee or percentage of the cumulative net profit)

8.2.3. የክፍያው አይነትና ተመን የሚወሰነው ኮንትራክተሩ ያቀረበውን የክፍያ ሁኔታ፣ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ተመሳሳይ ልምድ በማየት፣ የሃገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ እና የውጭ ምንዛሬ በሚቆጥብ መልኩ ሚኒስቴሩ እና ኮንትራክተሩ በድርድር በሚደርሱበት ስምምነት መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**8.3. የኪራይ ኮንትራት (Lease) ሲሆን**

8.3.1. በኪራዩ የሚካተቱ ሐብቶች

8.3.1.1. ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወይም የድርጅቱ ቅርንጫፍ፣

8.3.1.2. የድርጅት ይዞታ የሆነ ቦታ ወይም በውል በኪራይ የተያዘቦታ፣

8.3.1.3. ሕንፃዎች፣ መሳሪያዎች፣ ወይም ሌሎች የድርጅቱ የሆኑ ንብረቶች ሊሆኑ ይችላሉ፤

### 8.3.2.. በኪራይ ስምምነት ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዮች

8.3.2.1. ድርጅቱን በበቂ ሁኔታ ለመለየት የሚያስችል መግለጫ:- የድርጅቱ ስያሜ፣ አድራሻ፣ ድርጅቱ የተሰማራበት የምርት/የአገልግሎት ዓይነት፣ የተፈቀደ ካፒታል መጠን

8.3.2.2. የሚከራየውን ንብረት ይዞታካርታ፣ የካርታ ቁጥር፣ የተሽከርካሪ ባለቤትነት፣

8.3.2.3. የኪራይ ክፍያ መጠንና የክፍያ ሁኔታ፣

8.3.2.4. የኪራይ ውሉ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣

8.3.2.5. አከራዩ ንብረቱን ሲያከራይ የሚኖርበት ግዴታዎች፣

8.3.2.6. ተከራዩ የተከራየውን ንብረት ሲጠቀም የሚያከብራቸው ግዴታዎች፣

8.3.2.7. በኪራይ ውል የተሰጠ ንብረት ወይም ሀብት አያያዝ ወይም አስተዳደር እንደዚሁም ከዚህ የሚመነጭ ግዴታን የሚያሳውቅ ዝርዝር፣

8.3.2.8 በድርጅቶች ይዞታነት ያለ መሬት ከንብረቶቹ ጋር በኪራይ የሚካተት ከሆነ የመሬት ግብር የመክፈል ግዴታ የማን እንደሆነ፣

8.3.2.9 የተከራዩ ንብረቶች የኪራዩ ጊዜ እንዳለቀ የሚመለስበት /ርክክብ የሚደረግበት ስርዓት/፣

8.3.2.10 በሚከራዩ ንብረቶች ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎች የድርጅቱ ንብረቶች ካሉ ንብረቶቹ አገልግሎት የሚሰጡበት ሁኔታ፣

8.3.2.11. በኪራይ ውል ጊዜ የአከራይ ንብረት ቢበላሽ፣ ቢጠፋ ወይም አገልግሎት መስጠት ባይችል የሚተካበት ሁኔታ፣

8.3.2.12. ተከራዩ በውል ጊዜ ውስጥ ተጨማሪ ንብረት በኪራይ ወይም በግዢ ወደ አከራይ ንብረት የሚያስገባበት እና በኃላ የሚመልስበት ስርዓቶች፣

8.3.2.13. የሰራተኞችን መብትና ጥቅም የሚመለከቱ ጉዳዮች።

### 8.3.3. በኪራይ ጊዜ የሚኖረው የባለቤትነት መብት

8.3.3.1. በኪራይ የተሰጡ ንብረቶች አከራዩ በንብረቶቹ ላይ ያለውን ባለቤትነት አይለውጠውም::

8.3.3.2 ተከራዩ የተከራየውን ንብረት ተጠቅሞ የሚያገኘው ገቢ የራሱ ይሆናል፡፡

8.3.3.3 ተከራይ የተከራየውን ድርጅት አከራይ በጽሑፍ ካልፈቀደለት በስተቀር ውሉን አሳልፎ ለሌላ ወገን መስጠት አይችልም፡፡

8.3.4. የኪራይ ተመን አወሳሰን፣

8.3.4.1 የሚከራዩ ንብረቶች በሚኒስቴሩ የዋጋ ትመና መመሪያ መሰረት ጠቋሚ የትመና የኪራይ ዋጋ ላይ ተመስርቶ በሚገኝ የጨረታ የኪራይ ዋጋ ወይም በጠቋሚ ዋጋ ላይ ተመስርቶ በሚደረግ ድርድር የኪራይ ተመን ሊወሰን ይችላል፡፡

8.3.4.2 በኪራዩ ውሉ ላይ ኪራዩ የማይለዋወጥ/ቋሚ ተመን ወይም እንደአስፈላጊነቱ የሚለዋወጥ መሆኑን በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

8.3.5. የኪራይ ውልን በግልፅ ስለማስታወቅ፣

8.3.5.1 ተከራይ የኪራይ ውል ስምምነቱን በሚመለከተው የምዝገባ ተቋም ማስመዝገብ አለበት፡፡

8.3.5.2 ተከራዩ በንግድ ወረቀቶች እና በሚፃፃፍባቸው ሰነዶች ላይ ሁሉ ተከራይነቱን "ተከራይ" በሚል ቃል እያስከተለ መግለፅ አለበት፡፡

9. የልማት ድርጅቶች ተሳትፎና ውጤት ማሳወቂያ ሂደት

9.1. ሽሪክን (ፓርትነርን) በጨረታ አወዳድሮ ማስገባት አስፈላጊ ሲሆን ከጨረታ ሰነድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ መጨረሻው ምርጫ ድረስ የልማት ድርጅቱ ማኔጅመንትና ቦርድ በቀጥታ እንዲሳተፉ ሚኒስቴሩ ሊያደርግ ይችላል፣

9.2 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንዳስፈላጊነቱ ሽሪክ (ፓርትነር) የመፈለግ፣ የመጋበዝ፣ የመገምገም እና የማስገባት የስልጣን ውክልና ለልማት ድርጅቶቹ ሊሰጥ ይችላል፡፡

9.3 የልማት ድርጅቶች የሽሪክ (የፓርትነር) ፍላጎት በማመንጨት ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

9.4 የፓርትነር የማስገባት ሂደት ላይ የሚደረስበትን የመጨረሻ ውሳኔ የልማት ድርጅቱ ለማስፈፀም እንዲችል እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## የሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) የትብብር ስምምነቶች

### 10.የሽርኪና የፓርትነርሺፕ የትብብር ስምምነቶች

10.1 የመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of Understanding):-

10.1.1. ሽሪክ (ፓርትነር) የተገኘለት የልማት ድርጅት ከሽሪኩ (ፓርትነሩ) ጋር በመነሻ ጉዳዮች ላይ መግባባት ሲደረስ በሚኒስትር እና በሽሪኩ (ፓርትነሩ) መካከል የመግባቢያ ሰነድ ይፈረማል፡፡

10.1.2 ይህ የመግባቢያ ስምምነት (Memorandum of Understanding)ወደ ሚቀጥለው ውል ዝርዝር ስራዎች ለመግባት የሚያዘጋጅና መተማመንን የሚያዳብር እንጂ የተዋዋይ ወገኖች የመጨረሻና አስገዳጅ የውል ሰነድ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡

10.2. ከሽሪኩ (ፓርትነሩ) ጋር የሚደረግ የውል (Partnership Agrement)

10.2.1 ይህ ስምምነት በሽሪኩ (ፓርትነሩ) እና በሚኒስቴሩ መካከል የሚደረግ ውል ነው፡፡

10.2.2 በውሉ ውስጥከተዋዋይ ወገኖች የሚጠበው መብትና እና ግዴታበግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡

10.2.3 ከውሉ የሚጠበቁ ውጤቶች በግልጽ በጽሑፍ መቀመጥ አለባቸው፡፡

10.2.4 በውሉ ውስጥ የተለያዩ ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ ጉዳዮች እንዳይኖሩ በተብራራ መልኩ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

10.2.5 የሚመሰረተው ሽርኪና (ፓርትነርሺፕ) አግባብ ያላቸውን የሀገሪቱን ህጎች ማክበር ግዴታ እንዳለበት በውል ስምምነቱ በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የሽርኪና (ፓርትነርሽፕ) ክትትል

የሽርኪና (ፓርትነትሽፕ) ትብብር የውል አፈጻጸሙን የመከታተል ኃላፊነት የሚኒስቴሩ ሆኖ የሪፖርት አቀራረቡ ከአንቀጽ 11 እስከ አንቀጽ 13 በዝርዝር በተጠቀሱት መሠረት ይሆናል።

### 11. የጋራ ልማት ኮንትራት ክትትል

11.1 የጋራ ልማት ኮንትራት ስምምነቱ ወደ ሕጋዊ አፈጻጸም እስከ ሚሸጋገር እና አዲሱ ድርጅት እስከሚቋቋም ድረስ በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ የድርጅቱ ቦርድና ማኔጅመንት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

11.2 የጋራ ልማት ምስረታው ነባሩን ልማት ድርጅት ሕጋዊ ሰውነት ሳይነካ አዲስ የሚፈጠርከሆነ ሽርኪናው (ፓርትነርሽፑ) የመጨረሻ ቅርጹን እስኪይዝ ድረስም ሆነ ከዚያ በኋላ ስላለው አፈጻጸም የድርጅቱ ቦርድና ማኔጅመንት ለሚኒስቴሩ የሩብ ዓመት ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

11.3 የጋራ ልማቱ ከተመሰረተ በኋላ የተመሰረተው አዲስ አክሲዮን ማህበር ቦርድና ማኔጅመንት በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ የአፈጻጸም ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

### 12. ማኔጅመንት ኮንትራት ክትትል

12.1 ድርጅት ወይም አክሲዮን ማህበር በኮንትራት ማኔጅመንት ሲተዳደር የልማት ድርጅቱ እንደነበር የሚቀጥል በመሆኑ የሥራ አመራር ቦርዱ ሥራውን በበላይነት ይቆጣጠራል።

12.2 ቦርድና ማኔጅመንት በኮንትራት አፈጻጸም በተቀመጠ የመቆጣጠሪያና የመለኪያ መስፈርቶች (Contract monitoring and measuring parameters) በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ አፈጻጸም ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

## 16. መመሪያውን ስለማሻሻል

ማናቸውንም በዚህ መመሪያ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ለሚኒስቴር ቀርቦ ሲፀድቅ ሥራ ላይ ይውላል።

## 17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ታህሳስ 10 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*አዲስ አበባ ታህሳስ 10 ቀን 2009 ዓ.ም.*

ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር

# ቀድሞ በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎች

# የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

## የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ መመሪያ

ነሐሴ 1997 ዓ.ም.

<u>አዲስ አበባ</u>

አባሪ 2. የተሽከርካሪው ወይም የመሣሪያው ዓይነት በገበያ ላይ ያለው ተፈላጊነት /ዓ/

| ዓይነት | "ዓ" |
|---|---|
| 1. አውቶሞቢል | 0.90 |
| 2. ስቴሽን ዋገን | 1.10 |
| 3. አውቶብስ /ትንሹም ትልቁም/ | 1.10 |
| 4. ፒክአፕ | 1.10 |
| 5. የጭነት መኪና /ማንኛውም/ | 0.95 |
| 6. መሣሪያ የጫነ መኪና | 0.85 |
| 7. ተሳቢ | 0.90 |
| 8. የአፈር መግፊያ መሣሪያ /እርዝ ሙቪንግ/ | 0.75 |
| 9. የድንጋይ ወፍጮ | 0.75 |
| 10. አስፋልት መደባለቂያ | 0.75 |
| 11. አስፋልት ማቅለጫ | 0.75 |
| 12. ኮንክሪት መደባለቂያ | 0.75 |
| 13. ኮንክሪት ቫይብሬተር | 0.75 |
| 14. ፓምፕ | 0.90 |
| 15. ኮምፕሬሰር | 0.85 |
| 16. ጄኔሬተር | 0.75 |
| 17. ክሬን /ታወር/ | 0.75 |
| 18. ፎርክ ሊፍት | 0.75 |
| 19. ሞተር ብስክሌት | 0.85 |
| 20. ትራክተር | 0.90 |
| 21. አጭዶ መውቂያ | 0.75 |

አባሪ 3. የተሰራበት አገር ተመራጭነት /ተ/

| የተሠራበት አገር | "ተ" |
|---|---|
| ○ ምዕራብ አውሮፓና አሜሪካ | 1.0 |
| ○ ጃፓን | 1.0 |
| ○ ሩሲያና ምሥራቅ አውሮፓ | 0.8 |
| ○ ሌሎች | 0.8 |

አባሪ 4. የሰራው ፋብሪካ /ሞዴሉ ተወዳጅነት/ "ፋ"

1. አውቶሞቢል፣ ስቴሽንዋገን፣ ሚኒባስ፣ ፒክአፕ

| <u>ሰሪው ፋብሪካ</u> | <u>"ፋ"</u> |
|---|---|
| 1.1 ማርሴዲስ | 1.25 |
| 1.2 ቶዮታ | 1.15 |
| 1.3 ኒሳን | 1.05 ለስቴሽንዋገን፣ ለፒክአፕና ሚኒባስ፣ 0.95 ለአውቶሞቢል |
| 1.4 አይሱዙ | 0.95 |
| 1.5 ሚትስቡሽ | 0.95 |
| 1.6 ማዝዳ | 0.95 |
| 1.7 ሆንዳ | 0.95 |
| 1.8 ሱዚኪ | 0.95 |
| 1.9 ፔገሮ | 0.95 |
| 1.10 ሬኖልት | 0.95 |
| 1.11 ቮልስዋገን | 0.95 |
| 1.12 አውዲ | 0.95 |
| 1.13 ቢኤም ደብሊው | 0.95 |
| 1.14 ኦፔል | 0.95 |
| 1.15 ፊያት | 0.95 |
| 1.16 ላንድሮቨር | 0.95 |
| 1.17 ፎርድ | 0.80 |
| 1.18 ላዳ | 0.80 |
| 1.19 ኒቫ | 0.80 |
| 1.20 ዳትሰን | 0.95 |
| 1.21 ሀውንዳይ | 0.90 |

2. የጭነት መሣሪያ /ትራክ፣ አውቶቡስ

| <u>ሰሪው ፋብሪካ</u> | <u>"ፋ"</u> |
|---|---|
| 2.1 ማርስዲስ | 1.20 |
| 2.2 ፊያትና አይቪኮ | 1.20 |

| | | |
|---|---|---|
| 2.3 | ቮልቮ | 1.10 |
| 2.4 | ስካንያ | 1.10 |
| 2.5 | ዳፍ | 1.10 |
| 2.6 | ኒሳን | 1.00 |
| 2.7 | አይሱዙ | 1.00 |
| 2.8 | ሂኖ | 0.95 |
| 2.9 | ሚትስቡስ | 0.90 |
| 2.10 | ካማዝ | 0.80 |
| 2.11 | ብሉ በርድ | |

3. የአፈር መግፊያ መማሪያ /አርዝ ሙቪንግ/

| ሰሪው ፋብሪካ | | "ፋ" |
|---|---|---|
| 3.1 | ካተርፒላር | 1.2 |
| 3.2 | ኮማትሱ | 1.0 |
| 3.3 | ሚትስቡሽ | 0.9 |
| 3.4 | ድሬሰር | 0.8 |
| 3.5 | ፊያት አሊስ | 0.8 |
| 3.6 | ቻምፕዮን | 0.9 |
| 3.7 | ዋበኮ | 0.9 |
| 3.8 | ጋልዮን | 1.1 |
| 3.9 | ቮልቮ | 1.1 |
| 3.10 | ሚቺጋን | 1.0 |
| 3.11 | ሂታቺ | 0.9 |
| 3.12 | ካገዘ | 0.9 |
| 3.13 | ቱሲ ኤም | 0.9 |
| 3.14 | ፉሩካዋ | 0.8 |
| 3.15 | ሃኖማግ | 1.1 |
| 3.16 | ስካይ | 1.1 |
| 3.17 | ዳይናፓክ | 1.1 |
| 3.18 | ቦማግ | 1.1 |
| 3.19 | ኢንገርሶልራንድ | 1.1 |
| 3.20 | ሃይስተር | 1.1 |
| 3.21 | ቫይብሮማክስ | 1.0 |
| 3.22 | ማሪኒ | 1.0 |
| 3.23 | ቤተሲ | 0.9 |
| 3.24 | ሃም | 0.9 |
| 3.25 | አትላስ ኮፕኮ | 1.1 |
| 3.26 | ዴማግ | 1.1 |
| 3.27 | ኤቢጂ | 1.1 |

4. ሞተር ብስክሌት

| ሰሪው ፋብሪካ | "ፋ" |
|---|---|
| 4.1 ያማሃ | 1.1 |
| 4.2 ሱዚኪ. | 1.0 |
| 4.3 ሆንዳ | 1.0 |
| 4.4 ኡራል | 0.8 |
| 4.5 ሌሎች | 0.8 |

5. ትራክተር

| ሰሪው ፋብሪካ | "ፋ" |
|---|---|
| 5.1 ማሴ ፈርግሰን | 1.25 |
| 5.2 ፊያት | 1.00 |
| 5.3 ዜ.ቱ | 0.85 |
| 5.4 አይ ኤም ቲ | 0.85 |

6. አጭዶ መውቂያ

| ሰሪው ፋብሪካ | "ፋ" |
|---|---|
| 6.1 ጆን ዲር | 1.1 |
| 6.2 ዝማይ | 1.0 |
| 6.3 ኢ. 512/ ኢ. 514 | 1.0 |
| 6.4 ኒቫ ሲኬ 5 | 0.8 |

አባሪ 5. የተሽከርካሪው /የመሣሪያው ይዞታ/ "ይ"

1. መሣሪያው የሚሠራ ከሆነ መሣሪያው ያለበትን ሁኔታ በማገናዘብ ............ 0.7-0.8
2. መሣሪያው የማይሠራ ሆኖ ነገር ግን የመሣሪያው ዋና ዋና አካላትና ንዑስ አካላት (MAJOR COMPONENTS AND MAJOR PARTS) በመሣሪያው ላይ ያሉ ከሆነ መሣሪያው ያለበትን ሁኔታ በማገናዘብ .............................................. 0.5-0.6
3. የመሣሪያው ዋና ዋና ንዑስ አካላት (MAJOR PARTS) የጉደሉ ከሆነ እንደመሣሪያው ሁኔታ እንደጉደሉት አካላት ዓይነትና ብዛት ..................................... 0.3-0.49
4. የመሣሪያው ዋና ዋና አካላት (MAJOR COMPONENTS) የጉደሉ ከሆነ እንደመሣሪያው ሁኔታ እንደጉደሉት አካላት ዓይነትና ብዛት .............. 0.05-0.29